# የእድሳት ሂደት ፍሰት ቅጽ

## *በሂደቱ ስር ምን ላይ ነዎት?*

***ከእድሳትዎ ማብቂያ በፊት አውቶሜት የተደረገ ሂደቱ ይጀምራል። ጥቅማ ጥቅሞችዎ ስለመቀጠል አለመቀጠላቸው ወይም ወይም ተጨማሪ መረጃ የሚሰፈልገን ስለመሆኑ የሚገልጽ መረጃ ይደርስዎታል።***

ብቁ መሆንዎን የሚገልጽ ደብዳቤ ከደረስዎት ከቨርጂንያ Medicaid ጋር መቀጠልዎ ጥሩ ነው!

ቅጽ ወይም ማረጋገጫ ዝርዝር የሚደርስዎት ከሆነ እነዚህን ይሙሉና እስከ ማብቂያ ቀኑ ድረስ መልሰው ይላኩ [እድሳቱ ለCover Virginia በስልክ ቁጥር 1-855-242-8282 (TTY: 1-888-221-1590) ሊገባ ይችላል፣ በኦንላይን በCommonHelp.virginia.gov ሊገባ ይችላል፣ ወይም ለአካባቢዎ ኤጀንሲ በአካል እና በመልእክት/ፋክስ ሊገባ ይችላል – ከማረጋገጫ ዝርዝሩ የተወሰደ መረጃ በኦንላይን ወይም በአካል እና በመልእክት/ፋክስ ሊላክ ይችላል። ለምን ብቁ እንደሆኑ ለማየት እና መረጃዎን ሌላ የጤና ሽፋን ሊያገኙ ለሚችሉበት ለMarketplace ለመላክ ያስችለን ዘንድ መረጃዎን መልሰው መላክዎ በጣም አስፈላጊ ነው።

ቅጽዎንና ሁሉንም መረጃዎን መልሰው የሚልኩ ከሆነ ጥቅማ ጥቅሞችዎ ላይ ግምገማ እናካሂዳለን። ስለ ውሳኔያችን፣ እንዲሁም እንደተሳሳትን ካሰቡና እንዴት እንደሚዘጋጁ የተመለከተ መረጃ፣ እና መረጃዎ ወደ Marketplace የሚመራ ከሆነ መከተል ስለሚችሏቸው ተጨማሪ ደረጃዎች የሚገልጽ ደብዳቤ ይደርስዎታል።




ቅጽዎን ወይም መረጃዎን የማይመልሱ ከሆነ ጉዳይዎን "ባለማደስ" እንዘጋዋለን። ወደ Marketplace አይመሩም፣ ሆኖም ጉዳይዎ ከተዘጋ በኋላ እንደገና ማመልከት ሳይጠበቅብዎ መረጃዎን መልሰው የሚያስገቡበት ሶስት ወራት ይኖሩዎታል። መረጃዎን መልሰው ካስገቡና ብቁ ከሆኑ ጉዳይዎን ከተዘጋበት ጊዜ ጀምሮ መልሰን እንገመግማለን።